የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፬ኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ – ግንቦት ፫ ቀን ፲፱፻፺፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 35
ADDIS ABABA - 11th May, 1998

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፬/፲፱፻፺ ዓ.ም
የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የፈቃድ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..... ገጽ ፯፻፴፬

CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 34/1998
Private Employment Agency License Fees Council of Ministers Regulations ..... Page 734

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፬/፲፱፻፺

የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የፈቃድ ክፍያን ለመወሰን የወጣ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፬/፲፱፻፺ አንቀጽ ፲፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የፈቃድ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፬/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ ፡

፩. "አዋጅ" ማለት ስለግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፬/፲፱፻፺ ነው፡

፪. "የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ" እና "ፈቃድ" የሚሉት ቃላት በአዋጁ የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል።

፫. የፈቃድ ክፍያ መጠን

ማናቸውም የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ሆኖ በአዋጁ መሠረት ሥራና ሠራተኛን የማገናኘት አገልግሎት ለመስጠት የሚያመለክት አመልካች ለፈቃድ የሚከፍለው ክፍያ ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይሆናል ፡

COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 34/1998
REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE DETERMINATION OF LICENSE FEES FOR PRIVATE EMPLOYMENT AGENCY

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 19 of the Private Employment Agency Proclamation No. 104/1998.

1. *Short Title*

   These Regulations may be cited as the "Private Employment Agency License Fees Council of Ministers Regulations No. 34/1998."

2. *Definitions*

   In these Regulations:

   1) "Proclamation" means the Private Employment Agency Proclamation No. 104/1998;
   2) "Private Employment Agency" and "License" shall have the meanings given to them in the Proclamation.

3. *Amount of License Fee*

   The fees to be paid by any applicant intending to operate as a private employment agency, in accordance with the Proclamation, shall be as follows:

፩· ለፈቃድ ማውጫ ..... ብር ፫፻
፪· ለፈቃድ ማሳደሻ ..... ብር ፪፻
፫· ለፈቃድ መተኪያ ..... ብር ፪፻፶

፬· ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፺፣ ዓ·ም·

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

1) for issuance of license..... Birr 300.00
2) for renewal of license ..... Birr 200.00
3) for replacement of license..... Birr 250.00

4. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 11th day of May, 1998.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA